# refugee council
## help and advice

October 2006

# እቤት ውስጥ የሚፈጸም አመጽ – እርዳታ ይፈልጋሉን?

እቤት ውስጥ የሚፈጸም አመጽ የሚባለው፡ አብረው ከሚኖሩ ወይም ይኖሩ ከነበሩ ግለሰቦች መካከል ወይም በቤተሰቦች መካከል ወይም አንድ ቤት ውስጥ ኣብረው የሚኖሩ ጾታቸው ወይም ግኙንነታቸው ሳይመለከት የሚፈጸም ማንኛውንም ዓይነት የማስፈራራት፡ የመበደል ወይም አመጽ የማውረድ ተግባር ነው።

**የተለያዩ የአመጽ ድርጊቶች ይገኛሉ፡**

- አካላዊ አመጽ ማውረድ፡ ይህም እንደ መምታት፡ መርገጥ፡ መሳርያ በመጠቀም ወይም ያለመሳርያ መደብደብ፡ ማነቅ ወይም መውጋት የመሳሰሉት ለመጥቀሱ ይችላሉ።
- ጾታዊ አመጽ ማውረድ፡ ይህ ማለት ደግሞ በግድ የጾታዊ ግኙንነት መፈጸም፡ በጾታዊ የብልግና ተግባሮች/ፖርኖግራፊ ላይ በግድ እንዲመለከቱ ወይም እንዲሳተፉ ማድረግ፡ እና የጽንስ መከላከያ መድሃኒት ከመጠቀም መከልከል የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ።
- ሞራላዊ አመጽ ማውረድ፡ ማስፈራራት (እገድልሃለሁ ብሎ ማስፈራራት የሚያጠቃልል)፡ ንብረት ላይ አደጋ ማውረድ፡ መጨሀ፡ ማስፈራራት እና በቁጥጥር ስር መዋል የመሳሰሉት ያጠቃልላል።
- ገንዘባዊ አመጽ ማውረድ፡ ይህ ማለት ደግሞ የምግብ ወይም የገንዝብ እገዳ ማድረግ ነው።

**ማንኛውም ዓይነት አመጽ ከደረሰዎት፡ ቀጥሎ ያሉትን መረጃዎችን ማወቅ ይገባል፤**

- የደረስዎት በደል በተመለከተ ቀጥሎ ወዳሉት አካሎች ማመልከት ይገባል፡ ብሔራዊ በቤት የሚደረግ አመጽ የእርዳታ መስመር (National Domestic Violence Helpline)፡ ፖሊስ ጣብያ፡ እና የስደተኞች ምክር ቤት (Refugee Council)
- የሚያቀርቡትን መረጃ በሚስጢር የሚያዝ ሆኖ፡ ማንኛውንም የምንወስደው እርምጃ ደግሞ በስምምነትዎ መሰረት ይሆናል።
- ወደ ሌላ ቤት (ከነልጆችዎ) ለጊዜየው እንዲቆዩ ለማድረግ እንደሚቻል ማወቅ ይገባል።
- በግልዎ የጥገኝነት ጥያቄ ማቅረብ እንደሚችሉ ማወቅ ይገባል።
- የሚቀርቡት የአመጽ ማመልከቻዎች እንደ ከባድ ጉዳይ ያታያሉ፡
- ህጉ ደግሞ አመጽ ከሚያወርደው አካል ሊከላከልሎት ይችላል፡ ለምሳሌ ህጋዊ እርምጃን በመውሰድ
- እንዲሁም ሁኔታዎን ታይቶ ከ ብሔራዊ የጥገኝነት ድጋፍ አግልግሎት (National Asylum Support Service (NASS)) የሚያገኙትን እርዳታ ሊቀጥልሎት ይችላል።
- አመጽ የደረስዎት ምክንያት የራስዎን ጥፋት ሆኖ አይደለም፡

**እርዳታ ለማግኘት ቀጥሎ ያሉትን አካሎች ማነጋገር ይገባል፡**

**የ24 ሰዓት ነጻ የሆነው የብሔራዊ በቤት የሚደረግ የአመጽ እርዳታ መስመር በስ.ቁ**
**0808 2000 247** መደወል ይገባል። እንግሊዘኛ የማይችሉ ከሆኑ፡ የሚናገሩትን ቋንቋ መግለጽ አለብዎት፡ ሆኖ ግን አስተርጓሚ እስኪገኝ ድረስ መጠበቅ አለብዎት። ሌላው መንገድ ደግሞ የሚናገሩትን ቋንቋ በመግለጽና ስልክ ቁጥርዎን በመተው አማካሪው ወይም አስተርጓሚው መልሶ ይደውልሎታል።



Registered charity no. 1014576 Registered company no. 2727514 Registered address: 240-250 Ferndale Road London SW9 8BB

**ፖሊስ (አስቸኳይ ከሆነ) (Police (emergency)) 999**

**የስደተኞች ምክር ቤት የእርዳታ መስመሮች፡ የሚመለከተውን ቢሮ በስራ ሰዓቶች ውስጥ ይደውሉ፡**

| | |
|---|---|
| London | 020 7346 6777 |
| East of England | 01473 297 900 |
| West Midlands | 0121 620 1515 |
| Yorkshire & Humberside | 0113 386 2210 |


Registered charity no. 1014576 Registered company no. 2727514 Registered address: 240-250 Ferndale Road London SW9 8BB